ምስጋና ለኢየሱስ ሳይሆን ለእግዚአብሔር
ከኦቦ አራዳ ሻውል

ሕዳር 13 ቀን 2002

**መግቢያ**

ይኸን አርእስት ለምን ተመረጠ? ለመሆኑ በሁለቱ ስሞች ልዩነት አለው ወይ? መልሱን ለአንባቢያን ትቸዋለሁ።

ቅድስት ማርያም ልጅዋን ለማዳን ስትል በተለያዩ ስሞች ልጅዋን እየሱስ ትጠራው እንደነበር ይታወቃል።

የኢሕአፓ አባሎችም ሆኑ ደጋፊዎች ከአደጋ ለመዳን ሲባል የተለያዩ ስሞች እንደነበራቸው እሙን ነው።

ኢሕአፓ ከጅምሩ ጀምሮ የፖለቲካ አብዮት ለማካሄድ ተነሳ። ሆኖም ተቃሚያዎቹና ጠላቶቹ በጊዜው ሲያራምዱት የነበረ ፕሮፓጋንዳ የኢሕአፓ አቃም ፀረ- ሀይማኖት፤ፀረ- አንድነት፤ ፀረ- ሰላም፤ ፀረ- ጭቁኖች ፀረ-ፀረ የሚል ሲሆን የመጠሪያ ቅጽል ስሙም "አናርኪስት" "ገንጣይ-አስገንጣይ" "የኢዲዩ ልጆች" " ቅምጥሎች" "የኢምፐሪያሊስቶች ቅጥረኞች የመሳሰሉት ሲሆን ነገር ጉዳዩ ግና ከዚህ ሁሉ የተለየ ነበር ነውም። በእኔ እምነት "የአብየን እከክ ወደ እምየ ልክክ" እንደሚባለው ሆነ። የኢሕአፓን ገጽታ በጥቂቱም ቢሆን እንደሚከተለው ላስረዳ።

**የዓሲምባ ገጽታ**

ዓሲምባ ማለት ቀይ ተራራ ማለት ሲሆን ተራራውም የሚገኘው በኢጋሜ አውራጃና በአከለ ጉዛይ የምትገኝ ተራራ ናት።ኢሕአፓ ለምን ተራራ መረጠ? ለዛውም ቀይ ተራራ። ለምን? ከእስትራተጂካዊ* ባሻገር ኢሕአፓ ዓሲምባን የመረጠበት ዋናው ምክንያት ከደጋ ወደ ቆላ በመኳዝ እንደ ክርስቶስ ቀይ ደሙን እያፈሰሰ ኤትዮጵያን** እና ኤትዮጵያውያንን በስነ ልቦና ፤ በሥነ ምግባርና በመተማመን እያነጸ ሰላምንና እድገትን ለማስፈን ነበር።አባሎቹ ከየትም ሕብተረሰብ እና ከየትም እምነት ተውጣጥተው በማያውቁት ቦታና ስፍራ በመተማመን ረጅም ጉዙዋቸውን የዛሬ አርባ ዓመት ገደማ ጀመሩ።በአንጻሩ ደግሞ በቓንቓ ብቻ ትግራይ ትግሪኚ ተባብለው እምነቱ (TRUST) እና ጽናቱ ሳይኖር አብረው ጉዙዋቸውን ጨርሰዋል***

የኢሕአፓ ድርጅት እንደሌሎቹ ነጻ አውጪ ድርጅቶች በጦርነት ሳቢያ ብዙሀን ኤትዮጵያውያን እየገደሉ ሳይሆን ራሳቸውን እየሰዉ የሌሎችን ሕይወት እያዳኑ እንዲጋዙ ተደርገዋል። የጦር መሳሪዎቻቸው ለመከላከል እንጂ ለማጥቂያ እንዳልነበረ መገንዘብ ያስፈልጋል። ለዚህም ነው የኢሕአፓ ሠራዊት "አንቂ-ሠራዊት" ተብሎ እንደሚታወቅ ብዙዎቹ ይስማማሉ።

በአብዮትና በጦርነት ያለው ልዩነት በጉልህ ታይተዋል። ነገር ግና አሁንም ሻዕቢያና ወያኔ ራሳቸውን በመሾም አብዮት እያካሄድን ነው ያሸነፍነው ብለው

ይመጻደቃሉ።ቢሆንማ ኖሮ ስቃይና ስደት በቆመ ነበር።ያለ ንቃት (ወዳጅና ጠላት ሳይለዩ) አብዮት የሚባል የለም።በደርግ፣ በወያኔ፣በሻዕቢያ እንዲሁም በሌሎችም መታየቱ አልቀረም።ምን ይሻለናል ወዳጅና ጠላት መለየት አልቻልንም!!!

የኢሕአፓ የመጀመሪያው ተግባር ማንቃት (ማስተማር) ሲሆን በሁለተኛው ደረጃ ማደራጀት ነበር እንጂ አስታጥቆ ማንቃት የሚባል ነገር የለም።ሻዕቢያና ወያኔ ግና ለብዙ ዘመናት በዓዲ የተደራጀውን የኤርትራና የትግራይ ሕዝብ በተሳሳተ እና በውሸት ፕሮፓጋንዳ ማለትም የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ፣ የአማራ ጭቆና እያሉ ሕዝቡን ኮሎኒያሊዝም ምን ማለትና ከማን ብለው በቅጡ ሳያስተምሩ እንዲሁም አማራ ለምን መጠላት እንዳለበት ሳይገልጹ አርሶ አደሩን (ለዛዉም በግዢ መሳሪያ)አስታጥቀው አዋደቁ/ተዋደቁ ።

በሌላ በኩል ደግሞ በምክረ "ሚኤሶን" የሚባል ድርጅት ያልነቁ ወዳጅና ጠላት መለየት የማይችሉ ሴትኛ አዳሪዎችን እና ቦዘኒዎችን በንቃት ሳይሆን በመሳሪያ የከተማውን ሕዝብ አስጨንቀው በስመ "ነጭ-ቀይ" ሽብር አሰሩ፣ገደሉ፣ አስገደሉ።

የዓሲምባ ተራራ እንዲሁም በዙሪያው ያሉ መንደሮችን (መኖኽሰይቶ) እና የዓሳውርታ ሕዝቦች  ለኤትዮጵያ የዴሞክራሲያ አርአያ ሆነው እንዳያገለግሉ በዘረኞችና በምንደኞች ምክንያት ኢሕአሠ ቦታውን ለቆት ሄደዋል። ሆኖም ጊዜው በሚፈቅደው መሳሪያ ዓሲምባ ዶት ኦርግ በማለት ትምህርታቸውን (ትግላቸውን) እያካሄዱ መሆኑን ተገንዝበናል። ዛሬም መፎክሮቻቸው የሚያቀነቅነው በባንዶች፣በአንጃ፣ በበታኞች፣በጸረ-አንድነቶች ሲሆን፣ እንዲሁም በመጠኑ "በሆዳሞች" ላይ ነው።

<u>የጠለምት ገጽታ</u>

ኢሕአፓ ትግሉን በመቀጠል ጠለምትን ምሽጉ በማድረግ አርሶ አደሩን አሁንም በማንቃትና በማደራጀት ተያይዞት ነበር ሆኖም አሁንም አስመሳዮችና ምንደኞች በመከታተል የኢሕአሠን ሰራዊት ለመበተንና ለማጥፋት በልዩ ዘዴ  ለመበተን በቅተዋል።

ብተናው የሚመነጨው በክሕደትና በማታለል ነበር፣ ይኸውም ወያኔዎቹ እኛ ነን ለእናንተ የቆምነው እያሉ የጎንደር፣ የወሎ፣ የጎጃምና የሸዋ ሕዝብ ማታለል ሲሞክሩ የሕዝቡ ጥያቄ "እናንተ ኢሕአፓዎች ናችሁ" ብለው ሲጠዩቁዋቸው ቶሎ ብለው "አዎን እኛው ነን" ይሉ እንደነበር በራሴ ያየሁትና የሰማሁት ጉዳይ ነው።

ለምን እንደዚህ ሆነ ሊባል ይችላል፣ ወያኔ ኢሕአፓ ውስጥ የነበሩትን ደካሞችና የስልጣን ጥመኞችን በማፈላለግ ኢድህን በሚል ድርጅት አሰባሰባቸው፣ስለሆነም አዲስ አባባ እስቲገቡ ድረስ ሳይነቃባቸው ቆዩ።አሁን ግና ስለ ኢድህን ታረክ ሁሉም የሚያውቀው ይመስለኛል።

አሁንም ኢሕአፓ የተነሳበትን ዓላማ ግቡን ሳይመታ እፍይታ ስለሌለው ትግሉን ቀጠለ ራሱን እያቃጠለ። ነገር ግና ከመቀጠሉ በፊት ጉባኤ አካሄደ፣ የጉባኤው ዋና አጀንዳ ትግላችን እንቀጥል ወይስ እናቁም በሚልው አርእስት ነበር። በአንድ በኩል የነበረው

ክርክር እንደሚከተለው ነበር " ድርጅታችን በብዙ አካባቢ ስለ ተመታ" እጅ እንስጥ ወደ ደርግ እንግባ፣ ወደ ውጭ አገር እንኮብልል የሚል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ "የጀምርነውን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ መቀጠል አለብን የምናቆመው ሰላምና ብልጽግን በአገራችን ኤትዮጵያ ሲነግስ ብቻ ነው የምናቆመው" የሚል ነበር።

ስለሆነም በኢሕአፓ አሰራርና እምነት ዴሞክራሲያዊ አሰራር የተከተለ ሰለነበረና ስለሆነ አባሎቹም በፍላጎት የተገነቡና ያመኑ ስለነበር እንደየ ፍላጎታቸው ነጎዱ።

ድርጅቱ ግና እንደወትሮው ረጂም ጉዞውንና ትግሉን ቀጠለ አሁንም ራሱን እያቃጠለ። ነገር አለሙ ተቀይሮ ከመቅጽበት መንግስቱ ህ ማርያም ከአገር ሲያሸሹት አሁንም ለመጨረሻ ጊዜ ኢሕአፓን ከለንደኑ ስብሰባ ባለማሳተፍ ብቻ ሳይወሰኑ ከቻራ ተራራና ከበለስ በረሀ እንዲደመሰስ አሴሩ። እንደሚባለው የወያኔ፣ የሻዕቢያና የሱዳን ወታደሮች በመተባበር አጠፍዋቸው። በዚህ ጊዜ ነበር ደብተራው የተያዘውና ተስውሮ የቀረው።

እንደዛውም ሆኖ እነሆ ኢሕአፓ አሁንም ለ18 ዓመታት በወያኔ ላይ በማነጣጠር ትግሉን ቀጠለ ራሱንም በመጠኑ እያቃጠለ።

ዛሬ ለኢሕአፓ ረጂም እድሜ ስለተሰጠ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ።ለምን ቢባል አባሎችም ሆኑ ደጋፊዎቹ የሕሊና ወቀሳ፣ የሰው ጥላቻ፣ የጣዕሳም ሆነ በሌላ ሳይሸማቀቁ ከማነኛውም ሕብረተሰብ ሆነ ሕዝብ ጋር መኖርም ሆነ መነጋገር ስለሚችሉ።የሕዝብ ከሕዝብ አብራክ የተገኙ ናቸውና በዚሁ እንድንኮራባቸው ይገባል እላለሁ።

## <u>የመርካቶ ገጽታ</u>

መርካቶ የሁሉም መገናኛና መናህሪያ ስለሆነች (ስለነበረች) ኢሕአፓም እንደሌላው ሁሉ መርካቶን መናህሪውና ምሽጉ አድርጓታል። ኢሕአፓ እውነትም የሕዝብ መሆኑን ያስመሰከረው በመርካቶ ስፍራና ቦታ ነበር አሁንም ነው። ኢሕአፓ በነጻ ገበያ ኮርቶ እንደሚንቀሳቀስ ያውቃል።የኤትዮጵያ ፖለቲካ ማስተካከል ፈለጉ እንጂ፣ ገበያውማ እንጀራቸው ነበር ነውም። አዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት ሳያቆሙ እንደማይተኙ እርግጠኛ ነኝ።

## <u>ኢሕአፓና አመራር</u>

ለኢሕአፓ አመራር ማለት ግለሰቦች ማለት አልነበረም አይደለምም።

1. በዘውድ(crown prince)
2. በጥይት (bullet)
3. ወይም በድምጽ ብልጫ (vote)

የቱ ይመረጣል ብለው አመራሮች፣አባሎች እና ደጋፊዎች በጊዜው የነበረው የኤትዮጵያን ሁኔታ በመገምገምና በተጨማሪም ለምጪው ትውልድና ዘመን የሚያስፈልገውን ደረጃ ስለደረሱበት ይሀ ሶስተኛው አማራጭ ማለት በድምጽ ብልጫ (ዴሞክራሲያ) ነው መፍትሔው ተባብለው ስለአመኑበት ከዛሬ አርባ ዓመት የጀምሩትን ትግል እነሆ ቀጥለውበታል። ለዚህም እግዚአብሔርንና ደብተራውን ትግሉን በማስቀጠላቸው በበኩሌ አመሰግናለሁ።

ኦ አምላክ! የኢ.ሕአፓ

- *መሪዎቹን ጭንቅላት - ለ- ጭንቅላት አነጋግራቸው፤*
- *አባሎችን ልብ - ለ- ልብ አስማማቸው፤*
- *ሠራዊቶቹን ዓይን - ለ - ዓይን እንዲተያዩ አድርጋቸው፤*
- *ኢ.ሕአፓን ከሕዝብ ጋር በመንፈስ ጠርንፋቸው።*
- *ኢ.መፋን ፈውሳቸው።*

**የኢ.ዙና ጉዳይ**

*ለመሆኑ ኢ.ዙና ምንድን ነበር? አሁንስ ይንቀሳቀሳል ወይ? አባሎቹ በብዛት አሁንም በሕይወት መኖራቸው የማይካድ ሀቅ ነው። ቢሆንም እንደውትሮው በድርጅት መዝገበ-ቃላት በማካበት፤ በፍልስፍና በመራመር፤ገንዘብ በማዋጣት፤ወይንም ሙያዎች እርዳታ ለኢ.ሕአፓ በቀጥታ አያደርጉም።*

*ምክንያቱም ጊዜው የመደናቆር ስለሆነ ነው፤*(information overflow) *ተብሎ ይታወቃል። ዓሳ ግማቱ ከጭንቅላቱ ይባል የለ? በአዲስ አበባና በአስመራ ላይ ያሉ መንግስታት ዕውቀትን*(knowledge) *የማይሹ በመረጃ* (information) *ብቻ የሚያስተዳድሩ ይመስለኛል።*

***<u>ማጠቃለያ</u>***

*እግዚአብሔር ሆይ!*
*በሁሉም ስፍራ የምትኖር*
*መንግሥትህ ለ“ጴንጤ ቆስቴ” የኢየሱስ ተከታዮች እንደሆነች ሁሉ*
*ለእግዚአብሔር ልጆችም እንድትሆን እንጸልያለን።*

*ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ፤ ደሙን አፍስሶ ክርስቲያኑን እንዳዳነ ሁሉ*
*ኢ.ሕአፓንም መርቀህ ኤትዮጵያውያንን እንዲያድኑ እንጸልያለን*
*የአመጸንኞች መንግሥታት እንደወደቁ ሁሉ*
*የወያኔ መንግሥትም እንደ ኤትዮጵያውያን አቆጣጠር በ* 2013 *እንደሚወድቅ ይሁን*
*ኤርትርና ኤትዮጵያም እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ* 2013 *እንዲዋሃዱ አድርግ*

*አሁንም ዐግመላኅን ባርክልን*
*ደብተራው’ንም ከሠይጣኖች አላቅቅልን አሜን።*
*ከጠረ* (MIC and Light) *ሁሉ ሰውረነ አሁንም አሜን።*

* ( ) ( )
* * =
* **

---- the route from the sea-level to the highest mountain